# እንደገና መግባት

## ተከራዮች፡ መብቶችዎን ይወቁ!

**የጀርባ ምርምራ በሚደረግቦት ጊዜ የወንጀል ጥፋት ቢገኝቦትና በዚህም ምክንያት ቤት ማግኘት ቢከለከሉ፣ የተጠቀሙበትን የምርመራ ውጤት ኮፒ የማግኘት መብት አልዎት።**
**አከራዮትን የምርመራውን ኮፒ በመጠየቅ በትክክል የእርስዎ መዝገብ ላይ ያለውን ማወቅ ይችላሉ።**

## የወንጀል ሪከርድ ካለብኝ ለMDHA የህዝብ መኖሪያ ቤት ወይም ለክፍል 8 ቫውቸር ብቁ እሆናለሁ?

ለMDHA የሕዝብ መኖሪያ ቤት ወይም ለክፍል 8 ቤቶች **በቋሚነት ብቁ እንዳይሆኑ** የሚያድርግዎት **ሁለት የወንጀል ጥፋቶች** ብቻ ናቸው፡

1. በድጎማ ቤቶች ውስጥ **የሜታፌታሚን ኬሚካል መሥራት**
2. **የዕድሜ ልክ የወሲብ ወንጀለኛ ምዝገባን** የሚያስከትል ማንኛውም ፍርድ

ከሁለቱ ጥፋቶች ውጪ በሆነና የወንጀል ማኅደርዎት ውስጥ በተገኘ ሌላ ጥፋት ምክንያት የMDHA የሕዝብ መኖሪያ ቤት ወይም የክፍል 8 ቤቶች ተከልክለው ከሆነ በዝርዝር ሁኔታዎቹ መሠረት **የቀረበው ውሳኔ ላይ ይግባኝ መጠየቅ የሚችሉበት እድል አለ**።

- ያለመስማማት ደብዳቤ **በጽሑፍ** እንዲሰጥዎ ይጠይቁ - **ከቤቶች ባለስልጣን ጋር መደበኛ ያልሆነ ውይይት** በማድረግ ያሉበትን ሁኔታ ማስረዳት የሚችሉበትን መንገድ ከዚያ ያገኛሉ።
- ጉዳዩ እልባት ማግኘቱን የሚገልጽ **የሚቀርብ ማስረጃ** ካልዎት ቀጣዩን ክፍል እንደ ምሳሌ ይመልከቱ።

## የግል ቤቶችስ?

የግል አከራዮች ከሕዝብ ቤቶች ወይም የክፍል 8 ቤቶች ጋር ተመሳሳይ የሆነ ህግ የላቸውም። በግል ማኅደርዎ ላይ በሚገኝ **ማንኛውም ዓይነት የወንጀል ጥፋት** ምክንያት ማመልከቻዎን ውድቅ ማድረግ ይችላሉ። ለግል ቤቶች ሲያመለክቱ ያሉበትን ሁኔታ **በአግባቡ ለማስረዳት** እና ችግሩ መፈታቱን ማረጋገጥ የሚችል **ማንኛውንም አይነት ማስረጃ** ለማቅረብ ይዘጋጁ። ማቅረብ ከሚችሉት ማስረጃዎች መካከልም፡

- ተቀጥረው ከሚሰሩበት ድርጅት ወይም ከሌላ ግለሰብ ለእርስዎ ድጋፍ የሚሰጡ **የምስክርነት ደብዳቤዎች**
- በተለያዩ **የማኅበራዊ ድጋፍ አገልግሎቶች** ላይ እየተሳተፉ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንደ ማገገሚያ ፕሮግራሞች ወይም አብያተ ክርስቲያናት
- ማንኛውም ጥፋተኝነትዎን እና ከዚያ በኋላም ለማሻሻል ያደረጉትን ነገሮች የሚገልጽ **ዝርዝር** ለምሳሌ ወደ ትምህርት መመለስ ወይም የበጎ ፈቃድ አገልግሎት

## አንዳንድ ጥፋቶች ከወንጀል መዝገብዎ ላይ ሊወጡ ይችላሉ።

የተወሰኑ ጥፋቶች ከወንጀል መዝገብዎ እንዲፋቁ ወይም **እንዲሰረዙ** ማመልከት ይችላሉ። እነዚህም **ጥፋተኛ ሆነው ያልተገኙባቸውን** ክሶች፣ **ወደ ክስ ያላመሩ** ጉዳዮችን እና ብይን ተሰጥቶባቸው **የተሻሩ ውሳኔዎችን** ያካትታሉ።

ከጥፋተኝነት ለመውጣት ብቁ መሆንዎትን ለማረጋገጥ ከፈለጉ ወደ ድረ ገጽ www.las.org በመግባት Reentry Screening Tool የሚለውን ክፍል ይጫኑ።

LEGAL AID SOCIETY (833) 837-HOME

NHBA

AMHARIC - Reentry

(615) 701-7957

AMAC American Muslim Advisory Council

(615) 988-6460

NASHVILLE CONFLICT RESOLUTION CENTER

ROOFTOP NASHVILLE

ይህ መረጃ ለዴቪድሰን ካውንቲ ብቻ ነው። እዚህ የቀረበው መረጃ የህግ ምክር አይደለም ወይም የህግ ምክር ለመመስጠት የታሰበ አይደለም። የሕግ ችግር ካጋጠመዎት፣ እባክዎን ለግል ጠበቃዎ ይደውሉ ወይም በአካባቢዎ የሚገኘውን የመካከለኛው ቴነሲ የሕግ ድጋፍ ማህበር እና የኩምበርላንድን ቢሮ በ1-800-238-1443 ይደውሉ ወይም የናሽቪል ሂስፓኒክ ባር ማህበር በ1-615-701-7957 ይደውሉ። 5/24 ተሻሽሏል።